## በአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ፅ/ቤት

## የ6ኛ ክፍል አከባቢ ሳይንስ ሁለተኛ አጋማሽ ሞዴል ፈተና (ሚያዚያ 2016 ዓ.ም)

**የፈተናው ሰዓት** - 1ሰዓት

**<u>አጠቃላይ ትዕዛዝ</u>**

በዚህ የአካባቢ ሳይንስ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛው መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይስጣል በፈተና ላይ የተሰጠውን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡ መልሱን የምትመልሱት በተዘጋጀው በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው፡፡ በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በዕርሳስ ብቻ ነው፤ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጠቆር አለበት፤የጠቆረውን መልስ መቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በሚገባ በማጥፋት መፅዳት አለበት፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰዓት 1 ሰዓት ነው፡፡ ፈተናውነ ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን ማጥቆሪያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናውን መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ(ኟ)እስከሚሰበሰብ ድረስ በቦታችሁ በመቀመጥ መጠበቅ አለባችሁ፡፡ መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናውን ሕግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም ፤ እንዳይፈተን ይደረጋል፡፡ ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት መልስ በመልስ መስጫው ላይ መሞላት ሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት፡፡

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም!**

1.በስተ ደቡብ አቅጣጫ የምስራቅ አፍሪካ ቀጠናን የሚያዋስን ሀገር የትኛው ነው

ሀ. አንጎላ ለ. ደቡብ ሱዳን ሐ. ቦትስዋና መ. ስዋዚላንድ

2.ቋሚና አግድም መስመርን በመጠቀም በዲግሪ ልኬት የሚገለፅ የመገናኛ አይነት ምን ይባላል

ሀ. ፍፁማዊ መገኛ ሐ. አንፃራዊ መገኛ

ለ. ንፅፅር መገኛ መ. አጎራባች መገኛ

3.ምስራቅ አፍሪካን የሚያዋስን የአፍሪካ ቀጠና የትኛው ነው

ሀ. ሰሜን አፍሪካ ሐ. መካከለኛው አፍሪካ

ለ. ደቡብ አፍሪካ መ. ምዕራብ አፍሪካ

4.ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ምስራቅ አፍሪካን በስተ ሰሜን አቅጣጫ **የሚያዋስን** የውሃማ አካል የቱ ነው

ሀ. የህንድ ውቅያኖስ ሐ. ሜድትራኒያ ባህር

ለ. የኤደን በህረ ሰላጤ መ. ፓስፊክ ውቅያኖስ

5.ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ስለ ጎግል ኧርዝ ትክክል **የሆነው** የቱ ነው

ሀ. የንግድ ትስስርንአቅጣጫን ይጠቁማል

ለ. ለጥናትና ምርምር አያገለግልም

ሐ. የመኪና ፍጥነትን ለመቆጣጠር ይጠቅማል

መ. የተፈጥሮ ሀብትን ለማየት እና ለመንከባከብ ይጠቅማል

6.በህዋ ላይ በተቀመጡና በመሬት ዙሪያ የሚሽከረከሩ ሰው ሰራሽ ሳተላይቶች አማካኝነት የመሬትን ትክክለኛ ገፅታ ለማሳየት የሚያገለግል መተግበሪያ የቱ ነው

ሀ. ጎግል ካርታ ሐ. ጎግል ኧርዝ

ለ. ቴሌ ግራም መ. ጂፒኤስ

7.የአውሮፕላንን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የሚያገለግል መተግበሪያ የቱ ነው

ሀ. ጂፒኤስ ሐ. ሉል

ለ. ጎግል ካርታ መ. ጎግል ኧርዝ

8.ስለ ደም ስር ትክክል **ያልሆነው** የቱ ነው

ሀ. ደም ቅዳና ደም መልስን የሚየገናኝ የደም ስር አይነት ቀጫጭን የደም ስር ነው

ለ. ከሰውነታችን ደምን ወደ ልብ የሚመልስ የደም ስር አይነት ደም ቅዳ ነው

ሐ. ከልብ ወደ ሰውነታችን ደምን የሚያሰራጭ የደም ስር አይነት ደም ቅዳ ነው

መ. ደም የሚጓዘው በደም ስር ውስጥ ነው

9.ወደ ትልቁ ደም ቅዳ ደምን የሚረጭ የልብ ክፍል የቱ ነው

ሀ. ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ ሐ. ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ

ለ. ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ መ. ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ

10.በጉርምስና እና በኮረዳነት ወቅት በወንዶችና በሴቶች ላይ የሚታይ ተመሳሳይ አካላዊ ለውጥ የቱ ነው

ሀ. ድምፅ መጎርነን ሐ. ዳሌ መስፋት

ለ. ጡንቻ መፈርጠም መ. በብብት ስርና በብልት አከባቢ ፀጉር መብቀል

11.ለኦክስጅንና ለካርቦንዳይኦክሳይድ ወደ ደም ውስጥ መግቢያና መውጫ ሆኖ ያገለግላል

ሀ. ትንክረት ሐ. ዐብይ ትንቧ

ለ. ደቂቅ ትንቧ መ. ባላ ትንቧ

12.ጥቃቅን ቀዳዳዎች ባሉት ዕቃ ላይ የፈሳሽና ያልሟሙ የጠጣር ድብልቆችን ለመለየት የምንጠቀመው ዘዴ የቱ ነው

ሀ. ንጥረት ለ. ቀረራ ሐ. ጥሊያ መ. ትነት

13.በአይናችን ወይም በአጉሊ መነፅር በመታገዝ መለየት **የማይቻለው** ድብልቅ የትኛው ነው

ሀ. ደም ሐ. አየር

ለ. የውሃና የዘይት ድብልቅ መ. የአሸዋና የባቄላ ድብልቅ

14.ስለ ጉልበት ምንጭ ትክክል **ያልሆነው** የቱ ነው

ሀ. ታዳሽ የሆኑ እና ታዳሽ ያልሆኑ የጉልበት ምንጮች በመባል ይመደባል

ለ. ታዳሽ የሆነ የጎልበት ምንጮች ለአየር ብክለት መንስኤ ናቸው

ሐ. በቀላሉ ሊተኩ የሚችሉ የጉልበት ምንጮች ታዳሽ የጉልበት ምንጭ ይባላሉ

መ. ነዳጅ ታዳሽ ያልሆነው የጉልበት ምንጭ ምሳሌ ነው

15.ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ አንዱ ታዳሽ የጉልበት ምንጭ **አይደለም**

ሀ. የፀሐይ ብርሃን ለ. የከሰል ድንጋይ ሐ. ነፋስ መ. ውሃ

16.አንድን ነገር አጥብቆ ለማሰር የሚያገለግል የቀላል መኪና አይነት የቱ ነው

ሀ. መፍቻ ለ. መፈንቅል ሐ. ሽብልቅ መ. ሽክርክሪት

17.ከሚከተሉት የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ሀገራት መካከል በሙቀት ስርጭትን ከፍተኛ ላይ የምትገኝ ሀገር የቱ ነው

ሀ. ኢትዮጲያ ሐ. ሶማሊያ

ለ. ታንዛኒያ መ. ኬንያ

18.ከታህሳስ እስከ የካቲት በሉት ወራት ዝናብ የሚያገኝ የምስራቅ አፍሪካ አከባቢ የቱ ነው

ሀ. በምድር ወገብ አከባቢ ያሉ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት

ለ. የምስራቅ አፍሪካ ሰሜናዊ ክፍል

ሐ. ከምድር ወገብ በስተደቡብ የሚገኝ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት

መ. የምስራቅ አፍሪካ ምዕራባዊ ክፍል

19.ከሚከተሉት ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት **ያልሆነው** የቱ ነው

ሀ. እፅዋት ሐ. ውሃ

ለ. አየር መ. ቤት

20. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ስለ ማዕድን አጠቃቀም ተግዳሮት ትክክል **ያልሆነው** የቱ ነው

ሀ. በሙያው ያሰለጠነ በቂ ሰው አለመኖር

ለ. የቴክኖሎጂ እጥረት

ሐ. በቂ መሰረተ ልማት አለመኖር

መ. የሀገር ውስጥ ከፍተኛ ፍላጎት

21. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ለአፈር መሸርሸር መንስኤ **የሆነው** የቱ ነው?

ሀ. እፅዋትን በወንዝ ዳርቻ መትከል

ለ. ከብቶችን በተለያየ ቦታ ለግጦሽ ማሰማራት

ሐ. ተዳፋት ቦታን አግድም ማረስ

መ. ተራራማ ቦታን ለእርሻ መጠቀም

22. ከሚከተሉት ውስጥ የአፈር መሸርሸርን ለመጠበቅ **የማያገለግል** ዘዴ ነው?

ሀ. ደነና ሐ. ዘር ማፈራረቅ

ለ. ቁልቁል ማረስ መ. ማዳበሪያ መጠቀም

23.የምሥራቅ አፍሪካ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ተግዳሮት ውስጥ **የማይመደበው** የቱ ነው?

ሀ. በሀገሮች መካከል ፍትሀዊ የውሃ አጠቃቀም መኖር

ለ. ከፋብሪካ እና ከኢንዱስትሪ በሚወጡ ፈሳሾች መበከል

ሐ. በውሃ አካላት ላይ የሚጨመሩ ኬሚካሎች መብዛት

መ. ድርቅና የአየር ንብረት መቀያየር

24. ለደን መጨፍጨፍ ምክንያት **ያልሆነው** የቱ ነው ?

ሀ. ዘመናዊ የእርሻ መስፋፋት　　　ሐ. የደን መቃጠል

ለ. የከተሞች መስፋፋት　　　መ. የህዝብ ቁጥር መቀነስ

25. ከሚከተሉት ውስጥ ለማዕድን መመናመን ምክንያት **የሆነው** የቱ ነው?

ሀ. ማዕድን ፍቃድ ባላቸው ማሕበራት ማስወጣት

ለ. ማዕድን ከውጣ በኃላ በአግባቡ አገልግሎት ላይ ማዋል

ሐ. የአፈር መሸርሸርን መከላከል

መ. ማዕድንን ለግል ጥቅም ማዋል

26. ከሚከተሉት ውስጥ የምስራቅ አፍሪካ ሀገር **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. ዛምቢያ　　　ሰ. ጋና

ለ. ዙምባቡዌ　　　መ. ኮሞሮስ

27. ከሚከተሉት የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ሀገራት ውስጥ በህዝብ ብዛት አነስተኛዋ ሀገር ማን ናት?

ሀ. ሞሪሽየስ　　　ሐ. ሪዩኒየን

ለ. ሲሸልስ　　　መ. ማዳጋስካር

28. ስለ ኑቢያ ሥልጣኔ ትክክል **የሆነው** የቱ ነው?

ሀ. ኑባዊያን በአክሱም በቀኝ ተገዝተዋል

ለ. ኑባዊያን ከግብፅ ባርንት ከውጡ በኃላ የመሰረቱት መንግስት ኩሽ መንግስት ይባላል

ሐ. ኑባዊያን የመሰረቱት የመጀመሪያ ከተማ ሜሩይ ይባላል

መ. ኑባዊያን የሚታወቁበት ዋነኛ ምጣኔ ሀብት ግብርና ነው

29. በምስራቅ አፍሪካ የሚታወቁ የቅርስ ቦታዎች ውስጥ **የማይመድበው** የቱ ነው?

ሀ. የአክሱም ሐውልት　　　ሐ. የአስመራ ጥንታዊ ከተማ

ለ. የጥያ ትክል ድንጋይ　　　መ. የናይል ወንዝ

30. ከሚከተሉት የምስራቅ አፍሪካ የቅርስ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. የውጭ ምንዛሬ መቀነስ　　　ሐ. መጣንኔ ሀብታዊ ዕድገትን ማሳደግ

ለ. የፈጠራ ስራ ማጎልበት　　　መ. የወደፊት የእድገት አቅጣጫን መተንበይ

31. የምስራቅ አፍሪካ የማዕድን አጠቃቀም ከሚቀንሱ ምክንያቶች ውስጥ **የማይመደበው** የቱ ነው?

ሀ. በቅርሶች አጠቃቀም ዙሪያ በቂ እቅድ አለመኖር

ለ. በቂ የሆነ እንክብካቤ አለመኖርና ቁጥጥር ማነስ

ሐ. ብቁና የሰለጠነ ሰው መኖር

መ. ለተፈጥሮ እና ለሰው ሰራሽ አደጋዎች የተጋለጡ መሆን

32. ከምስራቅ አፍሪካ የቱሪዝም ሀብት መዳረሻ ቦታዎች ውስጥ ሰው ሰራሽ **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን

ሐ. የጥምቀት በዓል

ለ. ሶፍዑመር ዋሻ

መ. የሐረር ጀጎል ግንብ

33. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ስለ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ትክክል **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. የውጭ ምንዛሬን መጨመር

ለ. የስራ ዕድልን መፍጠር

ሐ. ከውጭ ሀገራት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከር

መ. ጥቅም ያለዋሉን መሬት ወደ ፓርክነት በመቀየር የሀብት ብክነትን መጨመር

34. ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት መካከል የተሻል የኢንዱስትሪ ምርት የምትታወቅ ሀገር ማን ናት?

ሀ. ኢትዮጵያ

ሐ. ኬኒያ

ለ. ዩጋንዳ

መ. ሩዋንዳ

35. በምስራቅ አፍሪካ ዐብይ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ **የማይመደበው** የቱ ነው?

ሀ. ቱሪዝም

ሐ. ግብርና

ለ. ሥርቆት

መ. ማዕድን ቁፋሮ

36. ስለ ኤች አይ. ቪ/ ኤድስ ትክክል **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. ደም በመለገስ አይተላለፍም

ለ. የሰው ልጅ ብቻ የሚያጠቃ በሽታ ነው

ሐ. በሽታው የሚመጣው በቫይረስ አማካኝነት ነው

መ. የነጭ የደም ህዋስን የበሽታ የመከላከል አቅም ያዳክማል

37. ሥርዓተ ትንፈሳን የሚጎዳ ጎጂ ዕፅ የቱ ነው?

ሀ. ጫት
ሐ. የተበከለ ምግብ

ለ. አልኮል
መ. ሲጋራ

38. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት **ያልሆነው** የቱ ነው?

ሀ. የወንድ ልጅ ግርዛት
ሐ. ግግ ማስወጣት

ለ. የሴት ልጅ ግርዛት
መ. ጠለፋ

39. በአካባቢያችን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳይከሰቱ ለመቆጣጠር የማያገለግል ተግባር የቱ ነው?

ሀ. ለማህበረሰቡ ግንዛቤ መስጠት

ለ. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት የሚፈፅሙ ሰውችን ለህግ አሳልፎ መስጠት

ሐ. ድርጊቱ የተፈፀመባቸውን ሰዎች ወደ ህክምና ቦታ መውሰድ

መ. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት እንዲፈፀም ማህበረሰቡን ማበረታታት

40. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ድርቅን ለመቋቋም **የማያገለግል** ዘዴ የቱ ነው?

ሀ. እህልን በጎተራ መርጎ ማሰቀመጥ

ለ. ድርቅን መቋቋም የሚችሉ እፅዋትና እንስሳትን መንከባከብ

ሐ. ባጭር ጊዜ የሚደርሱ የሰብል ዘሮችን መዝራት

መ. በቤት ጣሪያ ጭስ ላይ እህሎችን እንዲቀመጡ አለማድረግ